DISCOVER
ITS BEAUTY

ክፍል 3

# የእስልምና መሠረቶች

ዶ/ር ናጂ ኢብራሂም



## የእስልምና መሠረቶች

እስልምና ወደ ደስተኛ፣ እርካታ እና ዘላለማዊ ሕይወት መግቢያ በር እውነተኛ አምላክ በሆነው አላህ እና በመጨረሻው ነቢዩ ሙሐመድ በማመን እንደሆነ ያስተምረናል።

እስልምናም በአላህ እና በነቢያቱ ማመን ብቻ የአእምሮ ሰላም፣ ደስታ እና መዳን ለማግኘት በቂ እንዳልሆነ ይነግረናል! እርሱን **በብቸኝነት** በማምለክ፣ ትእዛዙን በማክበር እና መልካም ስራዎችን በመስራት የአላ ህን ፈቃድ መፈፀም አለብን።

በተጨማሪም፣ አላህ በርሱ ላመኑትና እርሱን በብቸኝነት ለሚያመልኩ እና መልካም ስራዎችን ለሰሩ ሰዎች ስላዘጋጀው ምህረት፣ ምንዳ እና ጀነት በቁርኣኑ ገልፆልናል።

- **እነዚያም ያመኑት በጎ ሥራዎችንም የሠሩት እነዚያ የገነት ጓዶች ናቸው። እነርሱ በውስጧ ዘላለም ዘውታሪዎች ናቸው።** (2:82)
- **እነዚያንምያመኑትንናበጎሥራዎችንየሠሩትንአላህ(ገነትን)ተስፋ አደረገላቸው። ለእነርሱ ምሕረትና ታላቅ ምንዳ አላቸው።** (5:9)
- **እነዚያ ያመኑና መልካም ሥራዎችን የሠሩ የፊርደውስ ገነቶች ለእነሱ መስፈሪያ ናቸው።** (18:107)




# የእስልምና ትርጉም

እስልምና ማለት አንድ አምላክ ለሆነው ለአላህ ፈቃድ መገዛት ማለት ነው። ስለዚህ በአላህ አንድነት ማመን **(ተውሂድ)**፣ እርሱን በብቸኝነት ማምለክ፣ ትእዛዙን ማክበር እና ለፈቃዱ መገዛት ለነብያት እና ለመልእክተኞቹ ሁሉ የተላከው የአላህ መልእክት ዋና ይዘት ነው። ይህ **'መገዛት'** የሚለው ቃል የዐረብኛው ቃል **'እስልምና'** ትርጉም ነው።

የአላህ ነቢያት እና መልእክተኞች ሁሉም አንድ ዓይነት መልእክት ስለሰ በኩ ሃይማኖታቸውም አንድ መሆን አለበት!

ቁርኣን **'እስልምና' (ለአላህ መገዛት)** የአደም እና የሐዋ እና የዘሮቻ ቸው እውነተኛ ሃይማኖት እስከ ቂያማ ቀን ድረስ መሆኑን ያረጋግጣል። ቁርኣንም እንዲህ ይላል፡-

- **አላህ ዘንድ (የተወደደ) ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው።** (3:19)
- **«የአላህ መንገድ እርሱ ቀጥተኛው መንገድ ነው፡፡ ለዓለማት ጌታ ልንገዛም ታዘዝን» በላቸው፡፡** (6:71)
- **(ከሓዲዎች) ከአላህ ሃይማኖት ሌላን ይፈልጋሉን? በሰማያትና በምድር ያሉ ሁሉ፤ በውድም በግድም ለርሱ የታዘዙ ወደርሱም የሚመለሱ ሲኾኑ።** (3:83)
- **«በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርኣን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማዒልና ወደ ኢስሐቅም ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወ ረደው በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌ ታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንኾን አመንን፤ እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን» በሉ።** (2:136)



የሚገርመው፣ የእስልምና ትርጉም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ ይላል፡-

- ለእግዚአብሔር ተገዙ ከእርሱም ጋር ሰላም ሁኑ፣ በዚህ መንገድ ብልጽ ግና ወደ እናንተ ይመጣል። (ኢዮብ 22:21)
- ለእግዚአብሔር ተገዙ። (ያእቆብ 4:7)

የእስልምና አስተምህሮት በአላህ ማመን - መልካም ስራዎችን እና የጽድቅ ስራዎችን ሳናደርግ - መዳንን እና ዘላለማዊ ህይወትን (ጀነትን) ለማግኘት በቂ እንዳልሆነ እንደሚነግረን ሁሉ፣ መጽሐፍ ቅዱስም እንዲህ ይላል፡-

- እኔ፣ ጌታ፣ ልብን እመረምራለሁ እና አእምሮን እመረምራለሁ፣ ለእያንዳንዱ ሰው እንደ ምግባሩ፣ እንደ ሥራው የሚገባውን ዋጋ ለመስጠት። (ኤርምያስ 17:10)
- ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ... ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው። (ያእቆብ 2፡24-26)



الله

# የእስልምና አተገባበር

በእርግጥም ሙስሊሞች በአላህ (እውነተኛው አንድ አምላክ) ማመን ብቻ ሳይሆን መልካም ሥራዎችንም ይሠራሉ። ኢሳ፣ ሙሐመድ እና ሁሉም ነብያት ያስተማሩትን እና ያዘዙትን ትእዛዛት ያከብራሉ፣ እነሱም በአንድ እውነተኛ አምላክ ማመን፣ ዱዓ ማድረግ፣ መስገድ፣ ፈጣሪን በማምለክ መንበርከክ፣ በግንባር መደፋት፣ መጾም እና ምጽዋትን በመስጠት ለወደፊት አንድ ነገር ላማድረግ ባሰቡ ግዜ "አላህ ቢሻ **(ኢንሻ አላህ)**" ይላሉ እና የሙሳን፣ የዒሳን፣ የሙሐመድን እና የነብያትን ሰላምታ የሆነውን "ሰላም በእናንተ ላይ ይሁን **(አሰላሙ አለይኩም)**" በመጠቀም ሀይማኖቱን ይተገብራሉ።

ይህ የሁሉም የአላህ ነብያት ድንቅ እና ውብ ሀይማኖት **'እስልምና' (ለአላህ መገዛት)** የሚለውን እውነት፣ አንድነት እና ዓለም-አቀፋዊነትን በግልፅ የሚያሳዩ ጥቂት ምሳሌዎች እና ማስረጃዎች ናቸው።

በተግባራዊ ሁኔታ አንድ ሙስሊም ወይም እስልምናን መቀበል የሚፈልግ ሰው በእስልምና የእምነት አንቀጾች እና መሰረቶች ማመን አለበት።



# ብቸኛው እውነታኛ አምላክ
# በሆነው በአላህ ማመን



**1. በአላህ (በፈጣሪ) ማመን** - በህልውናው፣ አንድነቱ (በአረብኛ፣ **ተውሂድ**)፣ በጌትነቱ፣ ልዩ በሆኑት ስሞቹ እና ባህሪያቱ፣ እና እሱ ብቻ አምልኮ እንደሚገባው ማመን ነው።

የተከበረው ቁርኣን እና ነቢዩ ሙሐመድ ስለ አንድ እውነተኛ አምላክ የአላህ ስሞች እና ባህሪያት አስተምረውናል። የአላህን ታላቅነት በፍፁም በአእምሯችን ልንገነዘበው አንችልም ነገር ግን ስለሱ ባወቅን መጠን እሱን መውደድ እና ማምለክ እንጀምራለን። ከአላህ ስሞች እና ባህሪያት ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

አላህ (ትክክለኛው የአምላክ ስም)፣ ጌታ፣ ብቸኛ እውነተኛ አምላክ፣ ሩኅሩኅ፣ አዛኝ፣ ፈጣሪ፣ ሉዓላዊው ጌታ፣ ቅዱስ፣ ንጹሕ፣ የተባረከ፣ የሰላም እና የፍጽምና ምንጭ፣ ፈራጅ፣ ሁሉን አዋቂ፣ ሁሉን ተመልካች፣ ሁሉን ሰሚ፣ ታላቅ፣ ሁሉን ይቅር ባይ፣ ከሁሉ የላቀ፣ የላቀ፣ እጅግ አፍቃሪ፣ እጅግ በጣም ቸር፣ ሰጪ እና እውነት ነው።

ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡- **“ፍፁም የውበት እና የፍፁምነት ባህሪያት የአላህ ናቸው። አላህ ውበትን ይወዳል።”**



**2.** እሱን እንዲያመሰግኑት እና እንዲታዘዙት በፈጠራቸው **የአላህ መላእክት ማመን።**

**3.** ለኢብራሂም፣ ለዳውድ፣ ለሙሳ እና ለኢሳ የተወረደውን የአላህን የመጀመሪያ ቃል ጨምሮ **በአላህ መፅሀፍት ማመን።** የተከበረው ቁርኣን ለነቢዩ ሙሐመድ የተላከ የመጨረሻው፣ ንፁህ እና ትክክለኛ የአላህ ቃል ነው።

**4.** በአደም፣ በኑህ፣ በኢብራሂም፣ በሙሳ፣ በመጥምቁ የህያ፣ በኢሳ እና በሙሐመድ ጨምሮ **በሁሉም የአላህ መልእክተኞች እና ነቢያት ማመን።** እንደውም አንድ ሙስሊም በሙሳ እና በኢሳ (በሌሎቹም) ከአላህ ዘንድ እውነተኛ አምላክ ከሆነው ፈጣሪ የተላኩ ነብያት መሆናቸውን ካላመነ እውነተኛ አማኝ አይደለም።

**5. በመጨረሻው ቀን፣** በፍርድ ቀን እና በተጠያቂነት **ማመን።** በዚያ ቀን የሰው ልጆች ሁሉ በአላህ እንደ እምነታቸው እና እንደ ተግባራቸው በአላህ ፍርድ ይሰጣቸዋል።

ከዚህ የአላህ ፍርድ በኋላ እነዚያ በአላህ ያመኑ እና መልካም ሥራዎችን የሠሩት በጀነት ውስጥ ደስተኛ እና ዘላለማዊ ሕይወት ያገኛሉ። እነዚያም በአላህ የካዱት መልካም ስራዎችን ያልሠሩትን እና ያመጹትንም (አላህ ከሻ) ወደ ጀሀነም ይጣላሉ።



# በእስልምና ውስጥ ስድስቱ የእምነት መስፈርቶች
(የቀጠለ)

**6.** አላህ **በወሰነው እጣ ፈንታ** እና በነገሩ ሁሉ የመጨረሻ እውቀቱ ማመን።

ነገር ግን ምእመናን በአላህ ላይ ስለሚተማመኑ፤ እነሱ ረክተዋል፣ ተብቃቅተዋል እናም አላህ ለነሱ የወሰነላቸውን ነገር ጥሩም ሆነ መጥፎ ለመልካም አድርገው ያዩታል። ቀውሶች ወይም ችግሮች ሲከሰቱ ተስፋ ላለመቁረጥ ወይም ላለመጨነቅ ይሞክራሉ። ይልቁንም ሁኔታቸውን ለማሻሻል የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ ነገር ግን ከሁሉም በላይ ለመጨረሻ እርዳታ፣ ድጋፍ እና ሽልማትን ለማግኘት ወደ አላህ ይመለሳሉ።

ይህ በአላህ እና በሱ ድንጋጌ ላይ ያለው ውብ እምነት በሙስሊሞች ላይ የሚደርስ ማንኛውም ችግር እና መከራ ቢኖርም ወይም ዛሬ በዓለም ላይ እየተፈጸመ ያለውን ወረራ፣ ሥራ እና መሬታቸው፣ ነዳጃቸው እና ሀብታቸው ላይ እየደረሰባቸው ያለው ግፍ፣ አድልዎ፣ ስም ማጥፋት ቢደርስባቸውም ለሙስሊሞች የአእምሮ ሰላም እና እርካታ ያመጣል።





# አምስቱ የእስልምና መሰረቶች

እስልምና ይህንን እምነት በተግባር እንድናውል ያስተምረናል። እና በአጠቃላይ ሙስሊሞች እና እስልምናን ለመቀበል የሚፈልጉ ሁሉ መልካም ስራዎችን ከመስራት በተጨማሪ እነዚህን አምስት መሰረታዊ መሰረቶች ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው።

**1. ሸሃዳ (የእምነት ምስክርነት)፦**

ይህ ምስክርነት በጣም አስፈላጊው ምሰሶ እና የእስልምና መግቢያ በር ነው። በአረብኛ ይህን ይመስላል፡-

**አሽ-ሀዱ አላ ኢላሀ ኢለላህ ወ አሽ-ሀዱ አነ ሙሀመደን ረሱሉላህ**

ትርጉሙም፥

**"ከአላህ በስተቀር በእውነት እና በብቸኝነት የሚመለክ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ ሙሐመድም የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ።"**

አንድ ሰው እስልምናን ለመቀበል በአፉ መናገር ያለበት የእምነት ምስክርነት ነው፤ የእስልምና እውነተኝነት፣ ውበት እና ቀላልነት በአንድ ላይ ይዟል።





**2. ሰላት (መስገድ)፡-**

ሰላት ሁሉም ሙስሊሞች በቀን አምስት ግዜ ሊሰግዷቸው የሚገባቸውን፣ የግዴታ ስግደቶችን ያመለክታል። እነዚህ የአምልኮ ሥርዓቶች መቆም፣ ማጎንበስ እና በግንባር መደፋትን፣ የቁርኣን ክፍሎችን ማንበብ፣ አላህን ማመስገንና ማውሳት፣ እና ምህረቱን እና ጀነትን መለመን የያዙ ናቸው።

የሰላት ውበት እና ኃይል መንፈሳዊ እድገትን፣ ስነ-ልቦናዊ ምቾትን እና ድጋፍን እንዲሁም እፎይታን፣ መረጋጋትን እና ለነፍሳችን፣ አእምሮአችን እና ለልባችን እርካታን ያመጣልናል። ሶላት በቀን እና በሌሊት መከፋፈሉ ሁሌም አላህን (ፈጣሪን) እንድናስታውስ ይረዳናል።

ለሰላቱ ተጨማሪ ውበት የሚያደርገው የአላህ ነብያት አደም፣ ኑህ፣ ኢብራሂም፣ ሙሳ፣ ኢሳ እና ሙሐመድን ጨምሮ ለአንድ እውነተኛ አምላክ ለአላህ ሰላት መስገዳቸው ነው። በሌላ አነጋገር ሙስሊሞች የነዚያን የአላህ ነብያት እና መልእክተኞች ፈለግ እየተከተሉ ነው።

በተጨማሪም የአላህን ውዴታ፣ ለእርሱ መገዛት፣ ራስን ለርሱ አሳልፎ መስጠት፣ ዱዓ ማድረግ፣ አንድነት፣ እኩልነት፣ ቅንነት፣ ትዕግስት፣ ትህትና እና የዋህነት የመሳሰሉ ሌሎች በርካታ ውብ ፅንሰ-ሀሳቦች በሰላቱ ይገለጣሉ።

በእርግጥም ቅን ጸሎት (ሰላት)፣ ዚክር (አላህን ማውሳት)፣ ኢስቲግፋር (ምህረትን መሻት) እና ዱዓ (ልመና) ወደ አላህ ብቻ ጥልቅ እና አስደናቂ የአዕምሮ ሰላም፣ የመረጋጋት እና የበረከት ቁልፎች ናቸው።



# አምስቱ የእስልምና መሰረቶች (የቀጠለ)

**3. ዘካት (ምጽዋት)፦**

ዘካት  የአንድን ሰው ሀብት የተወሰነ መጠን ለድሆች እና ለችግረኞች የመስጠት ግዴታ ነው። ንብረታችንን እና ገንዘባችንን ያነጻል፣ በተመሳሳይ ጊዜ ከስግብግብነት እና ከስቃይ ያነጻናል። በሀብታሞች እና በድሆች መካከል የጋራ ፍቅር እና መከባበር ጠንካራ ድልድዮችን የሚገነቡ መተሳሰብን እና መጋራትን ያስተምራል። በእርግጥም ድጋፍን፣ እገዛን፣ ትብብርን እና በአጠቃላይ ማህበረሰቡን ያበረታታል።





**4. ሰውም (መጾም)፡-**

ሳውም ማለት በእስልምና የረመዷን ወር ውስጥ ከንጋት ጀምሮ ጀምበር እስክትጠልቅ ድረስ ከማንኛውም ምግብ እና መጠጥ እንዲሁም ከግብረ-ስጋ ግንኙነት መከልከል ነው። ከፃም ውብ ጥቅሞች እና ትምህርቶች መካከል፡-

- መንፈሳዊ ጥቅም፡- ተቅዋ (የአላህ ፍራቻን) እና ቅንነትን እናዳብራለን። የረመዳን ፃም የአላህን እዝነት እና ምህረት ለማግኘት፣ከጀሀነም እሳት ለመዳን እና በጀነት ውስጥ ዘላለማዊ ህይወትን ለማግኘት ጥሩ እድል ይፈጥርልናል።
- ስነ-ምግባራዊ እና ስሜታዊ ጥቅሞች፡- በረመዳን ትምህርት ቤት (ፃም) ውስጥ በተለያዩ የአለም ክፍሎች ያሉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ያለፍላጎታቸው የሚደርስባቸውን ረሃብ እውቅና በመስጠት ተሞክሮ እናደርጋለን። ይህ እንድናካፍል፣ እንድንተሳሰብ እና ትሁት እንድንሆን፣ ለጋስ እና ደግ እንድንሆን ያነሳሳናል።
- ትምህርታዊ ጥቅሞች፡- ጾም ብዙ ትምህርት ያስተምረናል፤ ለምሳሌ እንደ ከመጠን በላይ መብላትን የመሳሰሉ መጥፎ ልማዶችን መለወጥ ወይም መተው እንደሚቻል እንገነዘባለን። ጾም ጠባያችንን ይገሥጻል እና ታጋሽ እንድንሆን እና ራሳችንን እንድንቆጣጠር ያሰለጥነናል። በተጨማሪም፣ እንደ ሙሐመድ፣ ሙሳ እና ኢሳ ያሉ የአላህ ነቢያትም ይጾሙ እንደነበር ያስታውሰናል።
- የጤና ጥቅማ ጥቅሞች፡- በፃም ሂደት ሰውነታችን መርዛማ ንጥረ ነገሮችን እና ተጨማሪ ቅባቶችን ያስወግዳል። ዶክተሮች እና የስነ ምግብ ተመራማሪዎች ብዙውን ጊዜ ጾምን እንደ 'ቆሻሻ ማቃጠያ' እና 'ፈውስ ህክምና' በማለት ይገልጹታል፣ እና ለተለያዩ በሽታዎች እንደ መድሐኒት ይመክራሉ።



Namirah Mosque
Mosquée De Namira
Nemire Mescidi
مسجد نمرة
مسجد نمرة

**5. ሐጅ (መንፈሳዊ ጉዞ)፦**

ሐጅ ማንኛውም ሙስሊም በአካል፣ በአእምሮ እና በገንዘብ አቅም እስካለዉ ድረስ በህይወት ዘመኑ አንድ ጊዜ ማከናወን ያለበት ወደ መካ የሚደረግ መንፈሳዊ ጉዞ ነው።

ልክ እንደሌሎቹ የእስልምና መሠረቶች ሁሉ የሐጅ ውበቶች፣ ትምህርቶች እና ጥቅሞች ብዙ ናቸው። የተለያየ ቀለም እና ዘር ያላቸው ከመላው አለም በሚሊዮን የሚቆጠሩ አማኞች የነቢዩ ኢብራሂምን ጥሪ ተቀብለው (ከባለቤታቸው ከሀጀራ እና ከልጁ እስማኢል ጋር) ከብዙ የሀጅ ሥርዓቶች ጋር የተቆራኙ ናቸው። በሐጅ ወቅት ድንቅ መርሆች እና ፅንሰ-ሀሳቦችን በተግባር ማየት ይቻላል፡ እነዚህም ለአላህ መገዛት እና መታዘዝ፣ በኢስላም ወንድማማችነት እና እህትማማችነት፣ አንድነት፣ ትዕግስት፣ መስዋዕትነት፣ ሰላት፣ ምጽዋት እና ፆም ናቸው። ዓመታዊው ሐጅ በዓለም ላይ ካሉት በዓይነቱ ልዩ የሆነ እና ትልቅ ሃይማኖታዊ ስብሰባዎችን ይመሰክራል እንዲሁም ያስተናግዳል።

በዚህ አስደናቂ የሁሉም ዘሮች እና ቀለሞች ውህደት ወቅት ሁሉም አንድ አምላክ ብቻ እያገለገሉ እና አንድ መልእክት ብቻ በመከተል ማልኮም ኤክስ እና ሌሎች የእውነተኛ እምነት ውበትን፣ ኢስላማዊ ወንድማማችነት እና እህትማማችነት እና እኩልነት አግኝተዋል።

ማልኮም ኤክስ እንዲህ ብሏል፣ **"የሀጅ ጉዞዬ አድማሴን አሰፋው። በአዲስ ግንዛቤ ባርኮኛል። በቅዱሱ ቦታ በቆየሁበት በሁለት ሳምንታት ውስጥ፣ እዚህ አሜሪካ ውስጥ በሰላሳ ዘጠኝ አመታት ውስጥ አይቼው የማላውቀውን አየሁ። በእውነተኛ ወንድማማችነት ሁሉንም ዘሮች፣ ሁሉም ቀለሞች - ሰማያዊ-ዓይን ያላቸው ብሉዝ እስከ ጥቁር ቆዳ ላሉ አፍሪካውያን አየሁ! በአንድነት! አንድ ሆኖ ሲኖሩ! አንድ ሆኖ ሲያመልኩ!"** (የማልኮም ኤክስ የሕይወት ታሪክ)

# በእስልምና ውስጥ የዋና ስሞች ፍቺዎች

**አላህ፡-** በአረብኛ አላህ ትክክለኛው የአንዱ እውነተኛ አምላክ የሆነዉ ፈጣሪ ስም ነው። እስልምና አላህ የሰው ልጆች ሁሉ እውነተኛ አምላክ እንደሆነ ያስ ተምራል።

**ሙሐመድ፡-** የአንዱ እውነተኛ አምላክ የመጨረሻው ነቢይ፣ ፈጣሪ የሆነው አላህ፣ ለሰው ልጆች ሁሉ የላከው ነው። ሙሐመድ ሰዎች ሁሉ አላህን (አምላ ክን) በብቸኝነት እንዲያመልኩ አዟል።

**እስልምና፡-** ለእውነተኛው አምላክ አላህ ፈቃድ መገዛት።

**ሙስሊም፡-** ለአንዱ እውነተኛ አምላክ አላህ ፈቃድ የተገዛ።

**የተከበረው ቁርኣን፡-** አንድ እውነተኛ አምላክ የሆነው የአላህ የመጨረሻ ቃል። ለነቢዩ ሙሐመድ የወረደ።

**መስጂድ፡-** ሙስሊሞች በዋናነት ለሶላት እና ለአምልኮ የሚጠቀሙበት ንፁህ የስግደት ቦታ ነው።



አላህ በአረብኛ



አላህን (እውነተኛውን አምላክ) የሚማፀን ሙስሊም



የተከበረው ቁርኣን



ሙሐመድ በአረብኛ

# የእምነት ምስክርነት (የእስልምና መግቢያ በር)

“ከአላህ በስተቀር በእውነት እና በብቸኝነት የሚመለክ ሌላ አምላክ እንደሌለ እመሰክራለሁ ሙሐመድም የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ።”

በአረብኛ እንዲህ ይነበባል፦


أشهد أن لا إله إلا الله وأشهد أن محمدا رسول الله


ሲነበብ ይህን ይመስላል፦

**አሽ-ሀዱ አላ ኢላሀ ኢለ ሏህ**

**ወ አሽ-ሀዱ አነ ሙሐመደን ረሱሉሏህ**

ይህ አንድ ሰው እስልምናን ለመቀበል በአፉ መናገር ያለበት የእምነት ምስክርነት ነው። የእስልምናን እውነተኛነት፣ ውበት እና ቀላልነት አንድ ላይ ይዟል።





DISCOVER

ITS BEAUTY

www.discoveritsbeauty.com

ይቃኙት

GLOBAL ACADEMY FOR TRANSLATION AND EDUCATION (GATE)
LONDON | THE UNITED KINGDOM

በAL-ANDALUS GROUP LTD የተተረጎመ
www.alandalusgroup.org

كتاب أبجديات الإسلام باللغة الأمهرية